# ሕግጋተ ወንጌል

በመግቢያችን ለመግለጥ እንደሞከርነው ሁሉ ስለሕግጋተ ወንጌል በሰፊው የመተንተን ዓላማ የለንም:: የዚህ መጽሐፍ ርእስ «ሕግጋተ እግዚአብሔር» የሚል በመሆኑና ከሕግጋተ እግዚአብሔርም ሶስተኛው ክፍል ሕገ ወንጌል ስለሆነ  የመጽሐፉን ይዘት የተሟላ ለማድረግና ለአንባብያንም የሕግጋተ እግዚአብሔርን ምንነት ለማስተዋወቅ እንዲቻል ሕገ ወንጌልን ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኗል:: ስለዚህም በዚህ ክፍል የሕግጋተ ወንጌልን ዝርዝርና ስለእያንዳንዳቸውም በአጭሩ ለማብራራት እንሞክራለን::

ለሕግጋተ ወንጌል ዝርዝር በቤተክርስቲያን መምህራን ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ:: አንደኛው ወገን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት ከቁጥር 22–45 የተዘረዘሩትን በመውሰድ እነዚህ ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል ናቸው በማለት የሚያስተምሩ ሲሆኑ፤ በሁለተኛው ወገን ያሉት ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሃያ አምስት ከቁጥር 35–36 የተዘረዘሩትን ስድስት ጥያቄዎች በመውሰድ ሕግጋተ ወንጌል እነዚህ ናቸው በማለት ያስተምራሉ:: በሶስተኛ ወገን ያሉት ደግሞ ሕግጋተ ወንጌልና ቃላተ ወንጌል የተለያዩ መሆናቸውን በመጥቀስ በማቴዎስ አምስት ያሉት ሕግጋተ ወንጌል ሲሆኑ በማቴዎስ ሃያ አምስት ያሉት ደግሞ ቃላተ ወንጌል ናቸው የሚል አመለካከት ያላቸው ናቸው::

የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ያለው አመለካከት ከሶስተኛው ወገን የሚስማማ ነው:: ሕግ ሲባል ለማድረግ የማዘዝና ከማድረግ የመከልከል ባሕርይ ያለው ከመሆኑ የተነሣና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት የተዘረዘሩት ሁሉ የሕግ ባሕርይ ያላቸው በመሆኑ ሕግጋተ ወንጌል ሊባሉ ይችላሉ:: በማቴዎስ ሃያ አምስት የተዘረዘሩትን ስንመለከት ደግሞ ከላይ የተጠቀሰውን የሕግ ባሕርይ አያንፀባርቁም:: ከዚህም ሌላ በዕለተ ምጽዓት ክርስቶስ በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት በይባቤ መላእክት በተገለጠና በፍርድ ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ ኃጥአንና ጻድቃን በግራና በቀኙ ቆመው እንዲመልሱ የሚያቀርብላቸው ጥያቄዎች ናቸው እንጂ በማዘዝ ወይም በመከልከል የቀረቡ ሕግጋት አይደሉም:: ስለሆነም ሕግጋት ከማለት ይልቅ ቃላተ ወንጌል ቢባሉ የበለጠ ተስማሚነው በሌላም በኩል እነዚህን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት የተዘረዘሩትን በተናገረ ጊዜ ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግጋተ ኦሪትን እያስታወሰ እየጠቀሰ መሆኑ ከሕግ ወገን ሕግጋት ለመሆናቸው በቂ ማረጋገጫ ነው:: ስለሆነም ሕግጋተ ወንጌል የሚከተሉት ናቸው:–

## 1.«በወንድምህ ላይ በከንቱ አትቆጣ»

ማቴ.5÷22–26:– ይህ ሕግ ወንድም የሆኑ የሰው ልጆችን ሁሉ የሚመለከት መሆኑን ልብ ማለት ያስጠ

ፈልጋል። በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ በመስቀል ላይ የተቆረጠ ሰውና የፈሰሰው የመድኃኔዓለም ሥጋና ደም ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ያደረገ የክርስትና መሠረት በመሆኑና በዚህ ቤዛነትም ለሰው ሁሉ ድኅነት በመስጠቱ ሁሉም ወንድማማቾች ሆነዋል። በመሆኑም ክርስቲያኖች አንዳቸው የሌላኛው አካላት ናቸውና አንዱ በሌላው ወንድሙ ላይ እንዳይቆጣ ታዝዟል። ከፍቅርና ከመተሳሰብ በቀር ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።

መቆጣት የሌላውን ሰው ስሜት የሚጎዳና ከቁጣው ድንገተኛነት የተነሣም ወደሌላ ከፍተኛ የስሜት ለውጥ ሊቀየር ስለሚችል ከመቆጣት መቆጠብ ተገቢ ነው። ያልታሰበና ያልተጠበቀ ቁጣ የደረሰበት ሰው በድንጋጤ ሊሞትም ይችላል። ከዚህም ሌላ በድንጋጤ ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ድርጊት የተነሣ ነፍስ እስከ መግደል ሊደርስም ይችላል። እንግዲህ ቁጣ በአንደበት የሚነገርና ቀላል ይምሰል እንጂ ውጤቱ አደገኛና አሳዛኝም ሊሆን እንደሚችል በማጤን ከመቆጣት መቆጠብና ቁጣንም ከራስ ማራቅ ይበጃል።

መቆጣት በሰው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት በተጨማሪ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላና ኃጢአትም በመሆኑ ከተፈጸመ በኋላ የሚከተለው ቅጣት አለ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለቀደሙት፡- አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፥ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፣ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።» በማለት ቁጣንና መሳደብን ከመግደል ጋር አስተካክሎ መግለጡ መቆጣት ከፍተኛ ኃጢአትና ቅጣቱም ታላቅ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ማቴ.5÷21-33። ስለዚህ ቁጣን ከራስ አርቆ በትዕግሥትና በመተሳሰብ መኖር ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚገባ ነውና ሁላችን ገንዘብ እናድርገው።

## 2.«ወደ ሴት አትመልከት በልብህም አታመንዝር»

ማቴ.5÷27። ይህ ወደ ሴት በመመልከት በልቡና የሚያድረው ፍትወተ ሥጋ ኃጢአት መሆኑን የሚያመለክት ነው። ሴትን ማየት ሳይሆን ባዩአት ጊዜ ለፈቃደ ሥጋ መመኘትን ነው እግዚአብሔር የማይፈቅደው። ለዚህም ነው በወንጌል «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛት ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል» በማለት የተነገረው። «ዓይቶ የሚያሰናክል ዓይን» የተባለውን ፍትወተ ተራክቦን አውጥቶ መጣልና መንግሥተ ሰማይን ገንዘብ ማድረግ በማየት የሚመጣ ምኞትን በመፈጸም በገሃነም ከመጣል ይሻላል፤ ይበልጣልም። ማቴ.5÷28።

ዓይን ሁሉን ይመለከታል፣ ወደልቡና መዝገብ የሚልከው ግን ቀልቡ ያረፈበትን ነው። በዚህ አንፃር ሴትን በክፉ የኃጢአት ምኞት መመልከት አይገባም፤ በልቡናም

ለዝሙትና ለተራክቦ ማሰብ ታላቅ በደል ነው፣ የሃሳብ መድረሻ ተግባር ነውና እርሱም ዝሙት:: ስለዚህ በማየት መዘዝ ከሚመጣ ውድቀት ለመዳን ይህን ሕገ ወንጌል በሚገባ መረዳትና ዓይነ ሥጋ ብቻ ሳይሆን ዓይነ ልቡናንም መቆጣጠር ያስፈልጋል::

## 3. «ሚስትህን ያለዝሙት ምክንያት በሌላ ነውር አትፍታት» ማቴ.5÷32

ይህ ሕግ ጋብቻ የከበረና መንፈሳዊ አንድነት ፍጹ ምም ተዋሕዶ ስለሆነ በተገኘው አጋጣሚና በተፈጠረ ችግር ሁሉ ሰበብ ሊናጋ የማይገባው መሆኑን የሚያመለክት ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል÷ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል÷ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ...ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም:: እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው::» በማለት ያስተማረው ትምህርት የጋብቻን ታላቅነትና ምሥጢራዊ ትርጉም የሚያስረዳ ነው:: ማቴ.19÷5-7:: በዚህ ትምህርት መሠረት ማንም ሰው ሚስቱን ለመፍታት አንዳች ምክንያት የለውም:: በሥነ ፍጥረትም ቢሆን ለአንድ አዳም አንዲት ሔዋን፤ ለአንዲ ት ሔዋን አንድ አዳም ብቻ የተፈቀደ መሆኑን ስንመለከት የምናስተውለው ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ የሚደረግ አንድነት መሆኑንና በቀላሉና በሰው ፍላጎት እንዳይፈርስ ሰማያዊና አምላካዊ ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑን ነው::

ይህን የከበረ አንድነት ማፍረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ በደልና ኃጢአት ነው:: ስለዚህ በፈቃደ እግዚ አብሔር አንድ የሆኑ ባልና ሚስት አንድነታቸውን አክብረው ሊጠብቁትና ከተቀደሰ ጋብቻ የሚለቀመውን መልካም ፍሬ በረከት ገንዘብ ለማድረግ መትጋት ይኖርባቸዋል::

ፈጣሪአችን እግዚአብሔር ኃጢአት በሆነ በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ጋብቻ እንዳይፈርስ አዝዟል:: መፋ ታት በተረጋገጠ የዝሙት ኃጢአት ምክንያት ካልሆነ በቀር የተወገዘ ነው:: ምክንያቱም ፍቺ ቤተሰብን ከመበተን አልፎ ከዚያ ጋብቻ የተገኙትን ሕፃናት የሚያጎሳቁል፣ ተስፋ ቢስ፣ ሰላምና ማኅበራዊ ፍቅርም የሌላቸው፣ በመጨረሻም ወደ

ኃጢአት ሥራ እንዲያዘነብሉና በነፍሳቸውም እንዲ ጎዱ ሊያደርጋቸው ስለሚችል ነው:: በዚህም የተነሣ ተስ ማምተው የተጋቡ ባልና ሚስት መፋታትም ሆነ መለያየት እንደማይገባቸው ዐውቀው በጋብቻቸው መጽናት አለባቸው::

## 4. «ፈጽመህ አትማል» ማቴ.5÷34:-

መሐላን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ስለመጥራት በተዘረዘረበት ክፍል በሰፊው የተመለከትነው

ስለሆነ ዳግመኛ ወደዚያ መመለስ አያስፈልገንም አልታ መነበትም። በአጭሩ ማንም ሰው በማንኛውም ጉዳይ ማረጋገጫ ለመስጠትና ባላንጣውን ለመርታት ወይም ተሟጋቹን ለማሳመን በማሰብ ቢምል ሕገ እግዚአብሔርን ያፈርሳል። በማንኛውም ምክንያት ቢሆን መማል ኃጢአት ነው። እንኳን በሐሰት በእውነት ነገርም ቢሆን መሐላ ፈጽሞ የተከለከለ ነው። የሚምል ሰው የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ ያደርጋል። ዘሌ.19÷12።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ በራስህም አትማል አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን፤ ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።» በማለት ያስተማረው ትምህርት መሐላን በጥብቅ ከልክሏል። ማቴ. 5÷33–37። የሚምል ሰውም ክፉ የተባለ የጠላት ዲያብሎስ ወገን መሆኑን በመግለጥ ከመማል እንድንቆጠብና ነገራችንን ሁሉ አዎን ወይም አይደለም በማለት እንድናጸና አስገንዝቦናል።

## 5.«ክፉን በክፉ አትመልስ» ማቴ.5÷39።

የዚህ ሕግ ዋና መልእክት ትዕግሥት ነው። በመታገሥ ወደኃጢአት ተግባር ሊያመራ የሚችለውን ሁኔታና ወደ ውድቀት የሚያደርሰውን የሥጋ ግፊት መቆጣጠር ይቻላል። ለሚያጋጥም ክፉ ፈተና በችኩልነት በግልፍተኝነት የሚደረግ አፀፋ ወይም ክፉን በክፉ መቃወም በዚህ ሕግ መሠረት የተከለከለ ነው።

በሌላ በኩል ይህ ሕግ በቀልን የሚቃወም ነው። «አትበቀሉ÷... በቀል የእኔ ነው÷ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮማ ክርስቲያኖች የጻፈው በወንጌል መድኃኒታችን «ክፉውን በክፉ አትቃወም» በማለት ካስተማረው በመነሣት ነው። ክፉውን በክፉ አለመቃወም ማለትም ክፉውን ነገር በክፉ ድል ለመንሣት አለመዘጋጀት፣ ክፉውን ግብር በክፉ ግብር አለመቃወም በጠቅላላው አለመበቀል ማለት ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ተወዳጆች ሆይ÷ራሳችሁ አትበቀሉ÷ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ» በማለት የተናገረው። ማቴ.5÷39። ሮሜ. 12÷17–19። ስለዚህ ክፉን በመልካም ማሸነፍ እንጂ በክፉ እንዳንሸነፍ ክፉውን ሃሳብ ከእኛ ማራቅ ይገባናል።

## 6.«ጠላትህን ውደድ»

ማቴ.5÷45፡- የዚህኛው ሕግ ዋና መልእክት ደግሞ ፍቅር ነው። ይህን ሕግ የሰጠን ክርስቶስ ጠላቶቹን በመውደድ እኛም እንዲሁ እንድናደርግ አስተምሮናል። ሰውን ሁሉ መውደድ የክርስትና ሕግ ነው። ይህ ሕግ ፍጹም የሚሆነው ደግሞ የሚያውቁትን ወዳጅን በማፍቀር ብቻ ሳይሆን ጠላትን በመውደድ በተግባር የተገለጠ እንደሆነ ነው። ክርስቶስ ሁሉንም በመውደድ በፍጹም ፍቅር እንደተገለጠ ክርስቲያኖች ሁሉ ደግሞ ሁሉን በመውደድ ፍጹማን እንድንሆን ይህ ሕግ ግድ ይለናል። ማቴ.5÷44–46።

ከዚህም በላይ በአጭሩ የቀረቡት ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል ሲሆኑ በዕለተ ምጽዓት ክርስቶስ ሰዎችን ሁሉ የሚመዝንባቸው ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የተራበን ማብላት ፡- ማቴ.25÷35።

ለ/ የተጠማን ማጠጣት፡- ማቴ.25÷35።

ሐ/ እንግዳን መቀበል ፡- ማቴ 25÷35።

መ/ የታረዘን ማልበስ ፡- ማቴ.25÷36።

ሠ/ የታመመን መጎብኘት ፡- ማቴ.25÷36።

ረ/ የታሠረን መጠየቅ፡- ማቴ.25÷36።

በእነዚህ ስድስቱ ቃላት አንፃር ክርስቶስ ለሌሎች የተደረገውን ሁሉ ለእርሱ እንደተደረገ፣ ለሌሎች ያልተደረገውን ለእርሱ እንዳልተደረገ በመቁጠር የምእመናንን ምግባር የሚመዝን መሆኑን እንገነዘባለን። በክርስቶስ ክርስቲያኖች የተባሉ የሰው ልጆች ሁሉ ማንንም ከማን ሳይለዩና ሳያበልጡ፣ ሳይንቁም እነዚህን ስድስቱን ምግባራት ለሁሉም በእኩል ሚዛን መፈጸም ይኖርባቸዋል። እነዚህን የፈጸሙትን መድኃኔዓለም ክርስቶስ «እናንተ የአባቴ ቡሩካን÷ኑ፣ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።» በማለት ዘለዓለማዊ የሆነውን የጽድቅ ዋጋ ይሰጣቸዋል። ማቴ.25÷34።

ስለዚህ እኛም ሕግጋተ ወንጌልን በመጠበቅና ቃላተ ወንጌልን በመፈጸም የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች ለመሆን እንድንበቃ በቸርነቱ ይርዳን። አሜን።